የከ/መ/ቁ 283433
ጥቅምት 30 ቀን 2013 ዓ/ም

ልደታ ምድብ 4ኛ ንግድ ችሎት

ዳኛ፡- መላ ነስሩ

ከሣሽ፡- ቤከር ጀነራል ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር - ጠበቃ አብይ መኮንን ቀረቡ
ተከሣሽ፡- ፊልማዊት የሕክምና ዕቃዎች አስመጪና አከፋፋይ - አልቀረቡም
መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሠጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

የከሣሽ ጠበቃ በአጭር ሥነ-ሥርዓት ታይቶ እንዲወሠን በየካቲት 12 ቀን 2012 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የክስ አቤቱታ ተከሣሽ ድርጅት ከከሳሽ ልዩ ልዩ መድሐኒቶችን በሽያጭ ገዝተው ክፍያው ሊፈፀምበት በተወሰነው ቀን የሚመነዘር የቼክ ቁጥሩ ቢሲ 3704764 የሆነ ብር 59,1630 (ሃምሳ ሦስት ሺህ ስድስት መቶ ሠላሳ ብር) ፣ ቁጥሩ ቢሲ 3704767 የሆነ ብር 90,551.20 (ዘጠና ሺህ አምስት መቶ ሃምሳ አንድ ብር ከ20/100)፣ ቁጥሩ ቢሲ 370469 የሆነ ብር 78,710.50 (ሰባ ስምንት ሺህ ሰባት መቶ አስር ብር ከ50/100 እና ቁጥሩ ቢሲ 3704770 የሆነ ብር 88,580.50 (ሰማንያ ስምንት ሺህ አምስት መቶ ሰማንያ ብር ከ50/100) የያዙ በንብ ኢንተርናሽናል ባንክ አክሲዮን ማህበር የረር በር ቅርንጫፍ በሚመነዘሩ ቼኮች ክያ የፈፀሙ ቢሆንም ቼኮቹ ለክፍያ ለከፋዩ ባንክ ሲቀርቡ ባንኩ በቂ ስንቅ የለውም የሚል የእንቢታ ማስታወቂያ በመስጠት ክፍያ ሣይፈጽም ተመልሰዋል፡፡ በመሆኑም ተከሣሽ በቼኮቹ ላይ የተመለከተውን ገንዘብ ብር 311,472.20 (ሦስት መቶ አስራ አንድ ሺህ አራት መቶ ሰባ ሁለት ብር ከ20/100) እንደሁም ከሣሽ በዚህ ክስ ምክንያት ያወጣቸውን ወጪዎች ጨምሮ እንዲከፍል ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቋል፡፡ በማስረጃነትም የቼኮቹን ኮፒ እና ባንኩ የሠጠውን ማረጋገጫ አቅርቧል፡፡

ተከሣሽም በህጉ አግባብ ጥሪ ቢደረግለትም በ10 ቀናት ውስጥ መከላከያ ማስፈቀጃ ያላቀረበ በመሆኑ ፍ/ቤቱ የመከላከል መብቱን አልፎታል፡፡

ፍርድ ቤቱም የከሳሽ ክስና ማስረጃ አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

ከሣሽ ክስ ያቀረበው ተከሣሽ እንዲከፈልበት የሠጠኝ ቼኮች ለክፍያ ለከፋዩ ባንክ ሲቀርቡ ሳይከፈልባቸው የተመለሱ በመሆኑ በቼኮቹ ላይ የተፃፈውን ገንዘብ ተከሣሽ ሊከፍለኝ ይገባል በማለት ሲሆን ለክሱ መነሻ የሆኑት ቼኮች በተከሣሽ ስም የወጡ መሆኑን እና ቼኮቹ ለክፍያ ቀርበው ባንኩ የእንቢታ ማስታወቂያ በመስጠቱ ሳይከፈልባቸው የተመለሱ መሆኑን የሚያስረዱ ማስረጃዎች ቀርበዋል፡፡

ከሣሽ ለክሱ መሠረት ያደረገው ጉዳይ ቼክ ሲሆን ቼክ ደግሞ በንግድ ህጋችን እንደ ንግድ ወረቀት ይቆጠራሉ ተብለው በን/ህ/ቁ 732/2/ ስር ከተዘረዘሩት የንግድ ወረቀቶች አንዱ ነው፡፡ ቼክ ከንግድ ወረቀቶች ውስጥ አንዱ ቢሆንም ከሌሎች የንግድ ወረቀቶች የሚለይባቸው ልዩ ባህሪያት ያሉት፣ ገንዘብን ተክቶ በስፋት አገልግሎት እየሠጠ ያለ፣ በንግድ ህጉ እንዲሁም በሌሎች ህጐቻችን ልዩ ጥበቃ የተሠጠው የንግድ ወረቀት ሲሆን ከነዚህ ልዩ ባህሪያት አንዱ ቼክ እንዲቀረበ የሚከፈልበት የንግድ ወረቀት መሆኑ ነው፡፡ ይህም በን/ህ/ቁ 854 ስር ተመልክቷል፡፡ የቼኩ አምጪ / Drawee / ቼኩን ለክፍያ ለከፋዩ ባንክ /Payee/ አቅርቦ ቼኩ ሳይከፈልበት ከተመለሰ የቼኩ አውጪ /Drawer/ ስለ ቼኩ አከፋፈል ዋስ በመሆኑ እና ገንዘቡን የመክፈል ሀላፊነት ያለበት በመሆኑ በቼኩ ላይ የተፃፈውን ገንዘብ የቼኩ አውጪ እንዲከፍለው መጠየቅ ይችላል፡፡ ይህም በን/ህ/ቁ 840 ፣ 868 ፣ 881 /1/ ስር ተመልክቷል፡፡

ከዚህ ላይ ደግሞ ተከሳሽ የቼኩ አውጪ በመሆኑ እና ይህ እንዲከፈልበት የወጣው ቼክም ሳይከፈልበት የተመለሰ በመሆኑ ተከሣሽ በን/ህ/ቁ 840 መሠረት ገንዘቡን የመክፈል ሀላፊነት

አለበት፡፡ የቼኩ አውጪ ከዚህ ኃላፊነት ሊድን የሚችለው ማለትም በቼኩ ላይ የተፃፈውን ገንዘብ ለቼኩ አምጪ የመክፈል ኃላፊነት የማይኖርበት፣ ቼክን መሠረት አድርጐ ለቀረበ ክስ በቼኩ አምጪ ላይ ሊቀርቡ ይችላሉ ተብለው በህጉ ተለይተው እና ተወስነው በን/ህ/ቁ 717 ስር የተቀመጡትን መከላከያ ምክንያቶች ያቀረበ፣ ይህን መከላከያ ምክንያቱንም ያስረዳ ሲሆን ነው፡፡ ይህ መከላከያም በን/ሕ/ቁጥር 717/1//3/፣ 849፣ 850 ስር የተቀመጠውን አይነት ከቼኩ አምጪ ጋር ያለውን የግል ግንኙነት መሠረት ያደረገ /Personal Relation Ship Defence/ ወይም በን/ሕ/ቁጥር 717/1/2/ ስር የተመለከቱት አይነት ከቼኩ አወጣጥ፣ ፎርም፣ የተፃፉ ቃላትና ፊርማ መሠረት ያደረጉ ቼኩን የሚመለከቱ መከላከያዎች /Real Defence/ ያቀረበ እና ይህንም መከለከያውን ያስረዳ ሲሆን ነው፡፡

ተከሣሽ በቼኮቹ ላይ የተመለከተውን ገንዘብ የከፈለ ወይም ሌላ የማይከፍልበት ምክንያት ያለ ስለመሆኑም በህጉ መሠረት ያቀረበው መከላከያ የለም፣ በተፋጠነ ስነ-ስርዓት ታይቶ እንዲወሠን ባቀረበው ክስ ተከሣሹ መከላከያ ካላቀረበ ክስ የቀረበበትን ገንዘብ ለከሣሽ እንዲከፍል ሊወሠን እንደሚገባ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 285/2/ ስር ተመልክቷል፡፡ስለሆነም ተከሣሽ ክስ የቀረበበትን ገንዘብ ለከሣሽ ሊከፍል ይገባል በማለት ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ው ሣ ኔ

1. ተከሣሽ ክስ የቀረበበት ገንዘብ ብር 311,472.20 (ሦስት መቶ አስራ አንድ ሺህ አራት መቶ ሰባ ሁለት ብር ከ20/100) ለከሣሽ እንዲከፍሉ ተወስኗል፡፡

2. ከሣሽ በዚህ መዝገብ ያወጣውን ወጪዎች በተመለከተ ለዳኝነት የከፈለውን ብር 5,995፤ ማስረጃ ለማስተርጎም እና የቴምብር ቀረጥ ለማስለጠፍ ብር 500 እንዲሁም ለጠበቃ አበል ክስ በቀረበበት ገንዘብ 7% ብር 22,015 በድምሩ ብር 28,510 (ሃያ ስምንት ሺህ አስራ አምስት ብር) ተከሣሽ ለከሣሽ ይክፈል፡፡

ት ዕ ዛ ዝ

- ይግባኝ ለጠየቀ መዝገቡ ተገልብጦ ይሠጥ፡፡
- መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡